# ራስ ሳይጠና ጉተና

**መሠረት ተፈራ** 12-10-14

የተጀመረው የእድገትና የልማት ጉዞ በአስተማማኝ መሠረት ላይ የተጣለ በመሆኑ ይቀጥላል፡፡ በሁሉም መስክ ያለው ሀገሪቷን ወደ ተሻለ የእድገት ደረጃ የማሸጋገሩና የማብቃቱ ሥራ ባለቤቱ ሕዝብ ስለሆነ ሊገታው የሚችል ምንም ኃይል የለም፡፡ የአባይን ግድብ እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን ሲል ሕዝብ ኃያልነቱን ደግሞ ደጋግሞ የማረጋገጡ እውነት ተጨባጭ ማስረጃ ነው፡፡

የፅንፈኛው ዳያስፖራም ሆነ በሀገር ውስጥ ያለው ተላላኪው የአመጽና የሁከት ሴራም ሆነ ሥራ ከሕልምነት አይዘልም፤ በሀገርና በሕዝብ ሕይወት የሚቀልድ ለውጭ ኃይሎች በመሣሪያነት የተሰለፈ በኢትዮጵያዊነት ስም የሚነግድ ተቃዋሚ ፓርቲ ምርጫ በመጣ ቁጥር ማንባረቁ የተለመደ ቢሆንም የተመኘውን ሊያሳካ በዶላር የተቀጠረበትን ሥራ ሊከውን አይቻለውም፤ በሕዝብ አመኔታም ቅቡልነትም የለውም፡፡

ዘጠኝም ሆኑ ሰላሳ ሦስት ፓርቲዎች ተቀናጅተውም ሆነ ተጣምረው፣ ተዋህደውም ሆነ መድረክ ፈጥረው ቀድሞ እንደሞከሩት ምርጫውን ተገን አድርገው የተለመደውን ድራማና ተውኔት በአልተለወጠ አስተሳሰብ በተቸከለና እልፍ በማይል የጥላቻና የስሜታዊነት ማዕበል ሰጥመው ሊወዛወዙ ይችላሉ፡፡

ዘጠኙም፣ ሰላሳ ሦስቱም ሆነ ሰባውም የአንድ ጠንካራ ፓርቲን ያህል በግልጽ የተሰመረ ፍኖተ ካርታ የሌላቸውና በየፊናቸው የሚባጁ ስለሆኑ ለሀገርና ለሕዝብም የሚበጅ መንገድ የላቸውም፡፡ በአንዲት ታዳጊና ደሃ ሀገር ላይ ሰባና ሰማንያ ተቃዋሚ ፓርቲ መኖር ማለት የውድቀት እንጂ የሀገር እድገትና የትንሣኤ ምልክት አይደለም፡፡

ለሕዝብም ለታሪክም አስረግጦ የሚነገረው እውነት በጋራ መቆም ባለባቸው ሀገራዊ ጉዳይ ላይ እንኳን ከመንግሥት እርስ በእርሳቸውም አብረው ለመቆም የማይችሉ በሀሳብ በፖለቲካ መስመር በእጅጉ የተለያዩ የተበጣጠሱ መቼም ወደ አንድ መስመር ሊመጡም ሊሰባሰቡም የማይችሉ መሆናቸውን ነው፡፡
ከዚህ በኋላም በርካታ የተቃዋሚነትን ስም የያዙ በቁጥር የበዙ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡በመካከላቸው ልዩነቱን እያሰፋው እያገዘፈው ይሄዳል እንጂ እያጠበበው አይመጣም፡፡

ወደ ኋላ ስንመለስ ከቀድሞው መአህድ ፓርቲ ብቻ የወጡ፣ ያፈነገጡ ወይንም የተለዩ ግለሰቦች ወደ ስድስት የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን መስርተዋል፡፡ ከኢዴፓ የወጡ ግለሰቦችም ሌላ ሦስትና አራት የተቃዋሚ ፓርቲ መስርተዋል፡፡

በቅርቡ ከተመሠረተው ኢራፓ ከሚባለው ፓርቲ እንኳን የተገነጠሉ አዲስ ራዕይ ፓርቲ ብለው አቋቁመዋል፡፡ ከአንድነት የወጡት እነ ኢንጂነር ይልቃል ሰማያዊ ፓርቲ የሚባል መስርተው ጥቂት ወጣቶችን አሰባስበው እንደኛ ያለ ፓርቲ በኢትዮጵያ አልታየም፤ አልተፈጠረም ሀገር ለመምራት በሚያስችል ቁመና ላይ ነን ሲሉ ሀፍረት የሚባል ነገር የላቸውም፡፡

የቀስተ ደመና ፓርቲ ታናሽ ወንድም የሆነው ሰማያዊ ፓርቲ መሪ ከእኔ በላይ ሌላ ፓርቲ የለም በሚለው እብሪት መወጠሩ ነባሮቹን አስቆጥቷል፡፡ ንቀቱና እብሪቱ አምባገነንነቱን ከፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማሪያም የወረሰው በመሆኑ ከውድቀት ሌላ ውጤት እንደሌለው ሁሉም ያውቃል፡፡

በዲያስፖራው አክራሪና በፕሮፌሰሩ እቅድ አውጭነት የት እንደነበሩ የማይታወቁ ዘጠኝ ኮክቴል ፓርቲዎችን ኢንጂነር ይልቃል ሰብስቦ በሊቀ መንበርነት ከተመረጠ በኋላ ተቃውሞ እንወጣለን 24 ሰዓታት ለአንድ ወር ወዘተ…እያለ ለኃይማኖት ተቋማትም ጥሪ ለማስተላለፍ ሞክሯል፡፡ የሚገርመው ያን ያህል በፖሮፓጋንዳ ያገዘፉትን የተቃውሞ ሰልፍ ለማካሄድ የተገኘው ሰላሳ ሰው ብቻ ነው፡፡ ኢንጂነር ይልቃልና ጥቂት ደጋፊዎቻቸውስ ይህን ቅዠት ምን ይሉታል?

ሕግን መጣስ የሚል መንገድ እንከተላለን ባይ ናቸው፡፡ ህግ ሲጥሱት ደግሞ የመጣስ አቅም አለው፤ አይጠፉቸውም፡፡ መድረክን ከመሠረቱት አንዱ የነበረው አንድነት ፓርቲ ስለፈፀምከው የደንብ መተላለፍ ይቅርታ ጠይቀህ ተመለስ ቢሉት የፈፀምኩት የለም አላደርገውም ከማለት አልፎ ምርጫን በተመለከተ አንድነት ፓርቲ በሌሎች ክልሎች ለምን ይሳተፋል በሚል የመድረኩ አባላት የሆኑ አንዳንድ ፓርቲዎች ያነሱትንም ነክሶ ይዟል፡፡

አረና፣ ኦፌኮ፣ ደቡብ ሕብረት፣ የሲዳማ ንቅናቄ ወዘተ… ብሄረሰቦች ላይ ያተኮሩ የክልል ፓርቲዎች ናቸው፡፡ ሰሞኑን ባደረጉት ምርጫ የዙር ሊቀ መንበርነቱን ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ተረክበዋል፡፡ የአንድነት ፓርቲና መድረክ አተካሮ እንዲህ በቀላሉ የሚቆም ባለመሆኑ ሰሞኑን በይፋ ተለያይተዋል፡፡

የቀድሞው የአንድነት ዋና ፀሐፊ የከሸፈው የሰላሳ ሦስት ፓርቲዎች ስብስብ ሊቀ መንበር የነበሩት አሥራት ጣሴ በቅርቡ ለአንድ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ ምልልስ መድረክ አንድነትን ማግለሉ የፖለቲካ ሴራ ነው ብለውታል፡፡

አንድነት ፓርቲ በራሱ የውስጥ ችግር እየታመሰ ሲሆን የቀድሞው ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ግዛቸው በውስጥና በውጭ ተፅዕኖ ነው ኃላፊነቴን እንድለቅ የተደረኩት፤ ዳያስፖራው ገንዘብ ስለሚረዳ ብቻ እኔ ባልኩት መንገድ ሂዱ የሚል የአስገዳጅነት ተጽዕኖ ፈጥሯል ባይ ናቸው፡፡

አዲሶቹ የአንድነት አመራሮች ደግሞ በውስጣችን ምንም ችግር የለም ቢሉም እውነቱ ግን የኢንጂነር ግዛቸው አብዛኛዎቹ ደጋፊዎች አሁን ቦታውን ለተረከበው አመራር እውቅናም ድጋፍም አለመስጠታቸው ነው፡፡ ይህም የአንድነት ፓርቲን ብቃትና ሕልውና በምርጫም የመሳተፍ አቅሙን እንደሚሸረሽረው ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

የአረናው ፓርቲ አባልና ወደ አንድነት አመራር የተቀላቀለው አብርሀም አሥራት በአንድነትም በመድረክም ያሉት ኢንጂነሮች፣ ዶክተሮችና ፕሮፌሰሮች በስም ጠቅሶ አሁን ላለው ትግል አስፈላጊ አይደሉም ይላል፡፡

የአብርሀም አሥራትና የነግርማ ሰይፉ አዲሱ የአንድነት አመራር ኢንጂነር ግዛቸው ኃላፊነት እንዲለቁ እኛም ግፊት እናደርግ ነበር ሲሉ ከምርጫው መቃረብ ጋር አዲስ አመራር መምጣት እንዳለበት መታገላቸውን ገልፀዋል፡፡

ዳያስፖራው ገንዘቡን እስካዋጣ ድረስ ሀሳቡን ተግባራዊ እንዲሆን ግፊት የማድረግና ተፅዕኖ የመፍጠር መብት አለው ነው የሚሉት አብርሀምና ግርማ ሰይፉ፡፡ ይህ ደግሞ በቀጥታ በሀገር ቤት ያለው የአንድነት ፓርቲ አመራር ራሱን ችሎ በነፃነት የሚንቀሳቀስና ውሣኔ የሚሰጥ ሳይሆን በዳያስፖራው ገንዘብ፣ ሀሳብና ውሣኔ የሚመራ ጥገኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እነሱም አምነው ተቀብለውታል ማለት ነው፡ ፡ የት ላይ ነው ታዲያ በሀገር ቤት ያሉት የአንድነት ፓርቲ አመራርና የአባላቱ ነጻነት ለሚለው ጥያቄ መልስ የለም፡፡ ነፃነት የሌላቸው መሆኑ እውነት ነው፡፡

ቀጣዩ እርምጃ ጽንፈኛው ዳያስፖራ ሰማያዊ ፓርቲንና አዲሱን የአንድነት አመራር እየነዳና እየጋለበ ትብብር፣ ግንባር እያለ አሰልፎ በዘጠኙ ፓርቲዎች ስም እንዲነግዱና እንዲንጫጩ ማድረግ ነው፡፡ ለጊዜው ዝም ቢሉም ይኼ ያለቀ ውሣኔ ስለሆነ በጥቂት ሣምንት ወይ በወር ውስጥ በተግባር የሚታይ ይሆናል፡፡ ጫጫታው፣ ወሬው፣ ፕሮፓጋንዳው፣ የፈጠራ ዜናው ሽብር መንዛቱን ሥራዬ ብለው ይቀጥላሉ፡፡

መኢአድም በራሱ የውስጥ ችግር እየተብላላ ነው፤ በቅርቡ ወደ አመራር የመጣው የነማሙሸት አማረ ቡድን በኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የተቀነባበረ ሴራና ተንኩል ከሕግ ውጪ ነው ሥልጣን የተረከበው፤ ኢንጂነር ኃይሉ ከመድረክ ላይ ጎትተው አውርደውኛል፤ የማይታወቁና አባል ያልሆኑ 150 ሰዎችን እነማሙሸት ወደ ጠቅላላ ጉባዔው አስገብተው አስቀድመው በተዘጋጁበት ድርጅታዊ ሥራ ድምፅ በማሰጠት ያለህጉ ያለደንቡ ከአመራር አውርደውኛል ሲሉ የቀድሞው ፕሬዚዳንት አቶ አበባው

መሐሪና አመራራቸው እንዲሁም ደጋፊዎቻቸው ለምርጫ ቦርድ ከሰዋል፤ አዲሱም የበፊቱም አመራር በየፊናቸው ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

የሚገርመው ነገር ልክ እንደሰማያዊ ፓርቲ ሊቀ መንበር እንደ ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት አዲሱ የመኢአድ መሪ ሆኖ የተመረጠው ማሙሸት አማረም ሀገር ለመምራት በሚያስችል ቁመናና አደረጃጀት ላይ ነን ሲል በድፍረት መናገሩ ነው፡፡ ይኼ ሀገር መምራት ያውም ሰፊዋን ኢትዮጵያን ለመምራት ማሰብ እንዴት ቀላል ተደርጎ እንደሚወሰድ የግለሰቦችም ግንዛቤ ቀልድ ነው ጨዋታ ወይንስ በሀገርና በሕዝብ ማሾፍ ነው ያስብላል፡፡

የየራሳቸውን ፓርቲ በቅጡ ሸክፈው መምራት ያልቻሉ፣ ልዩነቶቻቸውን በአግባቡ መፍታት የተሳናቸው፣ አምባገነንነት፣ ግብዝነት፣ ጀብደኝነት፣ ትምክህት የተጠናወታቸው ራሳቸውም በዚህ የሚኩራሩ ሰዎች እንዴት አድርገው ነው 90 ሚሊዮን ሕዝብ እንመራለን ብለው የሚያስቡት ያስብላል፡፡

ብዙዎች ተፈትነው የወደቁበትና የተንከባለሉበት ዋና ጉዳይ የአካዳሚ ማዕረጋቸውና እውቃታቸው መላቅና ትልቅነት ብቻ ለመሪነት የማያበቃ መሆኑን አለመረዳታቸው ነው፡፡ በተከበረው ሙያቸውና በእውቀታቸው ሀገራቸውንና ህዝባቸውን በምርምርና በማስተማር አገልግለዋል፤ አሁንም የበለጠ መሥራት ይችላሉ፡፡ በፖለቲካው መስክ ተደጋግሞ እንደታየው ግን ከውድቀትና ከመክሸፍ በስተቀር አልተሳካላቸውም፡፡

ሕዝቡን የማወቅና የመረዳት፣ የሕዝቡን ኑሮ የመኖርና ለሕዝቡ በቁርጠኝነት የመሥራት ፍላጐትም ዓላማም የሌላቸው ግን ደግሞ በእውቀታቸው የሚታበዩና እንዳሻን እንመራዋለን ብለው ማሰባቸው ነው ለውድቀትና ለክሽፈት ያበቃቸው፡፡ ህዝቡ ከእነሱ በላይ የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ አልሰማችሁም ሲላቸው ነው በአደባባይ ህዝብ ሆዳም ብለው እስከ መሳደብ የደረሱት፤ እነ ፕሮፌሰር መሥፍን ህዝብን የመሳደብ መብትም የላቸውም፡፡

ይህንን በመሰለ ትርምስምስ ውስጥ ተቃዋሚው ባለበት ሁኔታ ነው የ2007ቱ ብሄራዊ ምርጫ አፍጥጦ የመጣው የስድስት ወራት ጊዜ ብቻም የቀረው፡፡ ተቃዋሚዎች ይህንን መሠረታዊ ድክመታቸውን ለመሸፈን ሲሉ ብቻ ብቁ ነን፣ እንችላለን ችግር የለብንም ቢሉም ደረቁ እውነት ደግሞ በብዙ ሺህ የውስጥና የውጭ ችግሮች የተተበተቡና ተጠፍረው የተያዙ መሆናቸው ነው፡፡

ይኼ ከ40 ዓመታት በላይ በተለያየ ዘመናት ሥር ሰዶ የኖረው የተቃዋሚው ችግር ዛሬም አልተፈታ፡፡ ፈውስም መድኃኒትም አልተገኘለትም፡፡ በዚህ ውድቀትና ጥልቅ ችግር ውስጥ እየዋኙ ሀገርና ሕዝብ ለመምራት ብቁ ነን ሲሉ ያሳፍራሉ፡፡ ሀገር ታላቅ ቅርስና ክቡር ናት፤ መጫወቻና ማላገጫ አይደለችም፡፡

እንኳን የሀገርና የሕዝብ ችግርን ሊፈቱ ይቅርና የራሳቸውንም ችግር ለመፍታት አልበቁም ወይንም ሀገሪቱንም የበለጠ ውስብስብ ችግር ውስጥ ይዘናት አብረን እንውደቅ እንጥፋ የሚል እርኩሳዊ መንፈስ ነው የሚጋልባቸው ማለት ነው፡፡

ተቃዋሚው ትናንት በነበረበትም ሆነ አሁንም ባለበት ሁኔታ የቱንም ያህል በተናጠልም ሆነ በስብስብ፣ በቡድን፣ በጥምረት ወዘተ…የጋራ ጠላት የሚለውን ገዢውን ፖርቲ ለመጣል ብቻ ሺህ ቦታ ተበታትኖ ሲናቆር የሚገኝ በመሆኑ ሀገርንና ሕዝብን የመምራትና የማስተዳደር አቅሙም ብቃቱም የለውም፡፡ ህዝብም ኃላፊነት አይሰጣቸውም፡፡

ሕዝብና ሀገር ገና ሳይመሩ እርስ በእርስ እየተባሉ እየተናከሱ በጥላቻ በግብዝነት በአምባገነንነት እየተናነቁ ይፋጃሉ፤ ይጠፋፋሉ፡፡ እነዚህን ሥነ ምግባር ጨዋነት አርቆ ማስተዋልና ትዕግሥት መከባበር የሌላቸውን ኃይሎች ሀገር ምሩ ማለት ሀገር ትጥፋ፣ ሕዝብም ይተላለቅ፣ ሠላም አይኑር እንደማለት የሚቆጠር ነው፤ ከእብደትም የለየለት እብደት ነው፡፡

ተቃዋሚው የቆመበት የተለያየ የፖለቲካ አመለካከትና አስተሳሰብ እጅግ የተካረረ ፅንፍም በኃላፊነት ለመመረጥ የማያበቃው አንዱና ዋነኛው ችግር ነው፡፡

የሀገሩንና የሕዝቡን ሠላም፣ መረጋጋት፣ እድገትና ልማት ጠብቆ ለማስቀጠል በፍጹም የማይችል የማይበቃ አመኔታ የማይጣልበት ራሱን ከጨለማ ጉዞው የሚያላቅቅ መሪ የሚያስፈልገው ተቃዋሚ ነው፡፡ ለራሱ ሳይበቃ ሀገር ሊመራ የሚከጅል ደፋር ነው፡፡አባቶች እንዲህ ዓይነቱን ግብዝ ራስ ሳይጠና ጉተና ይሉታል፡፡